ስለ Omicron ይወቁ

የኮቪድ-19 ክትባት

# እውነታዎቹን ያግኙ።

## የኮቪድ-19 ልውጥ ቫይረሶች፦ ማወቅ ያለብዎት

ቫይረሶች ሁልጊዜ ይለወጣሉ። ትልቅ ለውጥ ሲከሰት ሳይንቲስቶች አዲስ ልውጥ ቫይረስ ብለው ይጠሩታል። አንዳንድ ልውጥ ቫይረሶች እምብዛም ጎጂ አይደሉም፣ ሌሎቹ ደግሞ አደገኛ ናቸው።



በቀላሉ ስዎቸን የሚይዙ እና ወደ ሌሎች የሚሰራጩ ወይም ለከፋ ህመም የሚዳርጉ ልውጥ ቫይረሶች ሳይንቲስቶችን ያሳስባሉ።



ጎልማሶችን፣ ታዳጊዎችን እና ልጆችን ጨምሮ፣ በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ብዙ ሰዎች በኮቪድ-19 ልውጥ ቫይረሶች ይታመማሉ።

## ክትባቶች ከልውጥ የኮቪድ-1 ቫይረሶች ይከላከላሉ።

እራስዎን፣ ቤተሰብዎን እና ማህበረሰብዎን ከልውጥ ቫይረሶች ለመጠበቅ ምርጡ መንገድ የኮቪድ-19 ክትባቶችዎን ወቅታዊ ማድረግ ነው። ክትባቶች፦

- **ደህንነቱ የተረጋገጠ፦** ክትባቱ የተለያየ ዘር፣ ጎሳ እና ዕድሜ ያላቸውን ሰዎች ጨምሮ በሚሊዮኖች በሚቆጠሩ ሰዎች ላይ ደህንነቱ የተረጋገጠ መሆኑ ተረጋግጧል። ከክትባቱ ይልቅ በኮቪድ-19 ምክንያት ከባድ ውስብስብ ችግሮች ሊገጥምዎት ይችላል።
- **ውጤታማ፦** ክትባቱ በኮቪድ-19 ልውጥ ዝርያዎች እንዳይጠቁ ጥብቃ ያድርግልዎታል። ክትባቱ በጠና ከመታመም እና ከታመሙ መሞትን ይከላከላል።
- **ነፃ፦** የኢሚግሬሽን ሁኔታዎ ምንም ይሁን ምን እንዲሁም መታወቂያ ወይም የሕክምና መድን ባይኑርዎትም ክትባቶች ለሁሉም ሰው ነፃ ናቸው።



ክትባቱን ወቅታዊ ካላደረጉ፣ በኮቪድ-19 የመያዝ፣ በአደገኛ ሁኔታ የመታመም ወይም የመሞት እንዲሁም ወደሌሎች የማዛመት ዕድልዎት ከፍተኛ ነው።

NRC-RIM
National Resource Center for Refugees, Immigrants, and Migrants

ለበለጠ መረጃ:cdc.gov/coronavirus

17 Aug 2022

# ክትባት በማግኘት አደገኛ የሆኑ ልዩነቶችን ማቆም ይችላሉ

ለሁሉም ማህበረሰቦቻችን ክትባት መስጠት አደገኛ የሆኑ ልውጥ ቫይረሶች መጀመርያውኑ እንዳይፈጠሩ የሚያደርግ አንደኛው የመከላከያ መንገድ ነው።

እራስዎን፣ ቤተሰብዎን እና ማህበረሰብዎን ከልውጥ ቫይረሶች ለመጠበቅ ምርጡ መንገድ የኮቪድ-19 ክትባቶችዎን ወቅታዊ ማድረግ ነው።

2 ሳምንታት

**ከክትባቶቹ ሊገኝ የሚችል ሁሉንም ጥበቃ ለማግኘት ከመጨረሻው ክትባትዎ በኋላ ሁለት ሳምንታት ይወስዳል።**

## ከኮቪድ-19 ልውጥ ቫይረሶች እራስዎን እና ማህበረሰብዎን ይጠብቁ

አንዳንድ የኮቪድ-19 ልውጥ ቫይረሶች ሰዎችን ለመያዝ እና ወደ ሌሎች ለመሰራጨት በጣም ቀላል ናቸው። ሙሉ በሙሉ በመከተብ እና በሚከተሉት መንገዶች እራስዎን እና ማህበረሰብዎን ይጠብቁ፦

- ጭምብል መልበስ።
- አካላዊ ርቀትን መጠበቅ።
- ከብዙ ሰዎች ጋር ስብሰባዎችን ማስወገድ።
- በፀረ ቫይረስ ማፅዳት ከፍተኛ ንክኪ ያላቸውን ቦታዎች
- እጆችዎን በተደጋጋሚ መታጠብ።



በመከተብ አደገኛ የሆኑ ልውጥ ቫይረሶችን ማስቆም ይችላሉ።

**ኮቪድ-19 ን ለማስቆም ያግዙ።**

NRC-RIM
National Resource Center for Refugees, Immigrants, and Migrants

ለበለጠ መረጃ:cdc.gov/coronavirus